# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 7 ቁጥር 5 ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም.

## ኢሕአፓ የትግል ትምህርት ቤት

*(ኢሕአፓ ለሕዝብ ይፋ የሆነበትን 45ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ* https://www.youtube.com/watch?v=WNbyDRThFsQ )

ያ ሕያው ዓላማ፣ ያ ዕጹብ ድንቅ ጅማሮ፣ ያ ብሩህ ተስፋ በወጣት አበባ ተከቦ ታጅቦ፤ የሽታው መዓዛ እጅግ መማረኩ ፈክቶና አብቦ፤ ተስፋውን ሰንቆ አደግሁ ለመለምኩ ብሎ ሳይጨርሰው፣ ጅማሬው ፍጻሜ ሁኖ ዛሬ ላይ አድርሶናል። ገና በጨቅላነት፣ ገና በልጅነት አገርን አስቦ፤ ሰንደቅ ዓላማ አንግቦ ከፍ! አርጎ ያስተጋባው የሕዝብን እሮሮ ዛሬም ይታወሳል ጉልህ ስፍራ ይዞ።

ኢትዮጵያ አገራችን በልጆቿ ለልጆቿ ትሆን ዘንድ፤ ዘር፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ ክልል አገሩ ኢትዮጵያ ሆና፣ ለበጎ ዓላማና ተልዕኮ ራዕዩን ሰንቆ ከተነሳው የ1960ዎቹ ትውልድ ውስጥ ከፍተኛውን የትግል ታሪክ ያስመዘገበው፣ የፖለቲካ ሀ ሁ አስቆጣሪው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዛሬ ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ የሆነበት 45ኛ ዓመት፤ እንኳን አደረሳችሁ!

በ1966 የካቲት አብዮት ዋዜማ መሠረቱን እንደጣለ የሚነገርለት ኢሕአፓ የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት ሳይዘጋጅና ሳይደራጅ ቢቀድመውም ትግሉ መሥመር እንዲይዝና የሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ በመላ አገሪቷ በአጭር ጊዜ መዋቅሩን በመዘርጋትና በማደራጀት፣ ሕዝባዊ መሠረት በመጣልና ኢትዮጵያዊነቱን በማጉላት “ኢሕአፓ” በማለት ያወጀበትን 45ኛ ዓመት ስናከብር የ“ያ ትውልድ” አባላት በተደበላለቀ ስሜት ነው። ሀዘን፣ ደስታ፣ ቁጭት፣ ጸጸት፣ ኩራት፣ መሰል ስሜቶች ይነዝሩናል። የት? መቼ? ለምን? ቦታ፣ ጊዜና ምክንያት ጠያቂ ቃላቶች ይወርሩናል። ያ የልጅነት፣ ያ የወጣትነት፣ ያ የተማሪነት፣ ያ የጎልማሳነት ትዝታ ወስዶ ከሙታን ሰማዕታት ጋር ያገናኘናል፣ ያላትመናል። ወንድም ጋሼ፣ ወንድም ጥላ፣ አለኝታዬ፣ መከታዬ፣ ላልነው ኢሕአፓ የተሽሎኮሎክነው፣ አደባባይ የጮህነው፣ ጋራ ሸንተረሩን፣ ሜዳ ኮረብታውን፣ ብርድና ሙቀቱን፣ ክረምትና በጋውን ይዘን የተጓዝነው፣ የበረሃው ተባይ፣ የከንፈር ድርቀቱ በውሃ ጥማቱ፣ ለሚላስ ሚቀመስ “ክስም[1]” ማጓጓቱ የትግል ትዝታ ሁኖ ይጋልበናል።

ኢሕአፓ የሕዝብ ጥያቄን መፈክሩ አድርጎ፣ የአገር እይታውን በፕሮግራሙ ቀርጾ፣ ትልቁ ሥዕሉን ዓላማውን ይዞ፣ በጀግና አባላቱ ግርማ ሞገስ ኮርቶ ያታገለና የታገለ ድርጅት ነው። የኢሕአፓ አባላት ጽናት፣ ቆራጥነት፣ እምነት፣ ታማኝነት፣ መለያቸው ነበር። ትግል ዓላማ መሆኑ በኢሕአፓ ተተግብሯል። ትግል ሕይወት መሆኑ በኢሕአፓ ታይቷል።

---

[1] ክስም ፡- በጎንደር ጠለምት ኅብረተሰብ ዘንድ በጋራ (በደቦ) ምግብ ከየቤቱ እየመጣ የሚመገቡበት የሚጨዋወቱበት ባህላዊ ክስተት

በኢ.ትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ጀግኖች አርበኞቻችን በከፈሉት ሕይወት ሀገራችን የግዛት ሉዓላዊነቷን፣ የሕዝብ አንድነቷን አስጠብቃ ለትውልድ ትሻገር ዘንድ አጥንታቸውን ከስክሰዋል፣ ደማቸውን አፍስሠዋል። የነሱ ክብር አገር፣ የነሱ መለያ ሰንደቅ ዓላማችን ነበርና ከጠላትና ወራሪ ጠብቀው ለትውልድ አስረክበዋል። "ያ ትውልድ" የተረከበውን አገርና ሰንደቅ ዓላማ ለሕዝብ በሕዝብ ይሆን ዘንድ የዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄን ከሕዝብ መንግሥት አስፈላጊነት ጋር አጣምሮ ቢ.ታገልለትም በደረሰበት የተቀነባበረ ምት ድሉ ውድቀት፣ ፍሬው ገለባ፣ አበባው ጠውልጎ፣ ልጆቹ አፈር ለብሰው ትዝታውን ታቅፎ፣ ሕያው ታሪኩን እየዘከረ ዛሬም አገሬን፣ ሕዝቤን እያለ ይተማል።

ኢ.ሕአፓ እጅግ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ከስህተት የጸዳ ነው ባይባልም ስንቁን ሰንቆ፣ ትጥቁን ከሽኖ፣ ፀጉሩን አጎፍሮ፣ እንስቶችን አሰልፎ "ፋኖ ተሰማራ!" ያለው ለአገር አንድነትና ለሕዝባችን ብሩህ ሕይወት እንደነበር በሙሉ አፍ መናገር ይቻላል። ኢ.ሕአፓ "ሕይወቴ ትግል"፣ "እምነቴ ፍጹም" ብሎ ጭቆናና ብዝበዛ ተወግዶ ድህነት፣ ድንቁርና በሽታ ቦታቸውን ለእድገትና ልማት ለቅቀው ኢ.ትዮጵያ ታሪካዊ ድምቀቷን፣ አብሪ ኮከብነቷን አስጠብቃ እንደ ዐድዋው ድል የዴሞክራሲን ድል ተቀዳጅታ ትጓዝ ዘንድ "ቼ! በለው" የዘመረ፣ ከአምባገነን ፋሺስት የተናነቀ ሕዝባዊ መሠረት የነበረው ብቸኛ ፓርቲ ነበር። ይህ ነው ታሪኩ!

ኢ.ሕአፓ ሲ.ታወስ ግጥም መዝሙሮቹ ዛሬም ያቃጭላሉ። አንች አዋሽ በረሃ፣ ማን ደባለቀው! ትግል ምኑን ትግል ሆነ! ማን ይፈራዋል! ደም! ግንባርህን አሳያቸው! እና ሌሎች ሕዝባዊ ግጥሞቹ የብዕር ተዋጊነትን በኢ.ሕአፓ መስክረዋል። ለዘመናት፣ እናንት መሪዎች፣ በትግል መሞት ሕይወት፣ አንቺ ጭቁን፣ ሰው በሀገሩ ሲበደል እና መሰል በርካታ መዝሙሮቹ ኢ.ሕአፓነትን አኩርተዋል። ሥነ ጽሁፍ የትግል ሞተሩ፣ የጥንካሬ መሠረቱ፣ የኢ.ሕአፓ ማንነቱ መገለጫ ለመሆኑ "**ዴሞክራሲያ** ዕትሙ ዛሬም ሕያው ምስክር ነች።

ኢ.ሕአፓ ሲ.ታውስ አጋዥ ቁሶቹ ከነፈጠራ ትንግርቱ ይታወሳሉ። አጥሮች መፊክሮቹን አስተናግደዋል፣ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች አርማውን አንጠልጥለዋል፣ የስልክ እንጨቶች በራሪዎችን ለጥፈዋል፣ "አደፍርስ" "**ዴሞክራሲያ**"ን አምርቷል ሌላም ሌላ።

ኢ.ሕአፓ ወጣቱን በኢ.ሕአወሊ፣ ተማሪዎችን በኢ.ተአድ፣ ሴቶችን በኢ.ሴትድ፣ እናት አባቶችን በቤተሰብ ሸንጎና በዴምክራቲክ ፍሮንት፣ ሕፃናትን በታዳጊ ወጣት፣ ወታደሮችን፣ መምህራንን፣ ሠራተኞችን፣ ላብ አደሮችንና አርሶ አደሮችን እንደ ሙያቸው ያደራጀና ያቀፈ ግዙፍ ፓርቲ ነበር። ኢ.ሕአፓ ከ"**ዴሞክራሲያ**" ዕትሙ ሌላ አብዮታዊ ወጣት፣ ላብ አደር፣ አርሶ አደር፣ ጭቁን ወታደር እና ሌሎች መሠል ወቅታዊ እትሞች ነበሩት። ኢ.ሕአፓ በከተማ ትግሉ የደርግን የ1967 ዓ.ም. የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻን ለማደራጀት ተግባሩ እጅግን ተጠቅሞበታል። የከተማውን እንቅስቃሴ ለማገዝ የቀበሌና ከፍተኛ መዋቅርን ተከትሎ ወጣቱን አደራጅቷል፣ ከሕብረተሰቡ ጋር በቀላሉ ተገናኝቷል። እራሱን ይፋ በአደረገ በአጭር ጊዜ በመላዋ ኢ.ትዮጵያ መሠረቱን የጣለ አንጋፋ ፓርቲ ነበር።

የኢ.ትዮጵያን አንድነት የሚፈታተኑ፣ ድብቅ ተልዕኮ የሚጫወቱ የአገር ውስጥና የውጭ ባዕዳን ኢ.ሕአፓን አልተፈታተኑትም ሊባል አይችልም። ይህ ለአገር ኩራት፣ የሕዝብ መሠረት የነበረ አንጋፋ ድርጅት ከውስጥ እየተሸረሸረ ከውጭ እየተከበበ ሲጓዝ ቆም ብሎ ማሰብ ተሳነው። ቤቱ እየተናደ፣ ጠላት እያየለ ሁኔታዎች የአካሄድ ለውጦችን ጠያቂ ቢሆኑም መሪ አላገኙም።

መንግሥቱ ኃ/ማርያም በ1969 ዓ.ም. ጥር 26 ቀን እነ ተፈሪ በንቲን እረሸኖ ከአቅራራ በኋላ፤ አደባባይ የተገበረውን ጠርሙስ ሰበራ ከቁብ የቆጠረው አልነበረም። የመስከረም 1969 ዓ.ም. በኢ.ሕ.አ.ፓ ላይ የታወጀው ጦርነት እየተንከባለለ ጥር 1969 ዓ.ም. በቁርስ የተጀመረው እርሸና የኢ.ሕ.አ.ፓውን ታላቅ መሪ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይን ሕይወት ቀጠፈ። በወዝ ሊግና መኢሶን ጣምራ ሤራ የተቀነባበረው የቤተ መንግሥት ፍጅት ለአደባባይ የቤት ለቤት አሰሳ፣ ነጻ እርምጃና ቀይ ሽብር በሩን ከፈተ። መልሕቋ እንደተበጠሰ መርከብ ኢ.ሕ.አ.ፓ በቤት-ለቤት አሰሳ ከፍተኛ እርከን ላይ የነበሩ ብርቅዬ አባላቱን አጣ፣ ነጻ እርምጃ መዋቅሩን እየበጣጠሰ አባላቱን መሂጃ መሸሸጊያ እያሳጣ ነጎደ። ቀይ ሽብር ወጣት የተባለን ሳይለይ ለእስር፣ ለሥቃይ፣ ለግርፍ፣ ለግድያ ዳረገ። ሕፃናት፣ አዛውንት እናትና አባቶች የጥቃቱ ሰለባ ሆኑ። በመኢሶን ዕቅድ አውጪነት ተግባራዊ የሆኑት የቀበሌና ገበሬ ማኅበራት የደርግ ዓይንና ጆሮ በመሆን በከተማ በአብዮት ጥበቃ፣ በገጠር በሚሊሺያ ኢ.ሕ.አ.ፓን "ለማጥፋት" ትውልድ የጨረሰ ዘመቻ ተካሄደ።

የነጻ እርምጃና ቀይ ሽብር ዒላማ የኢ.ሕ.አ.ፓ አባላት ላይ ያነጣጠረ ብቻ ሳይሆን ጅምላ የወጣት ፍጅት ሆነ። በ1969 ዓ.ም. አጋማሽ የ9ወር እርጉዝ ዳሮ ነጋሽ ተረሸና ጉድ! የተባለለት የግርማ ከበደን እርሸና የሚያስንቁ ፍጅቶች በመላ የኢትዮጵያ ከተሞች በተከታታይ ከሚያዝያ 1969 እስከ ሚያዝያ 1970 ተካሄደ። ኢ.ሕ.አ.ፓ ክፉኛ ተመታ። ያ ውብ ፓርቲ ከብሩህ አንደበቱ ጋር ተከተተ። ያ ፍቅር ፓርቲ ልጆቹን አጣ። ያ አለኝታ ፓርቲ መንፈስ ሆነ። ያ መከታ ፓርቲ ክንዴ ልጁን አጣ። ያ ጀግና ፓርቲ "የታጋይ ድምጽ ይጮሃል" እንዳለ ከመቃብር ጩኸት በረከተ። "በትግል መሞት ሕይወት" እንዳሉ በ100 ሺዎች አስከሬናቸው ለጅብና አሞራ ሲሳይ ሆነ። "ማን ይፈራል ሞት" ያሉት "ኢ.ሕ.አ.ፓ ያቸንፋል!" እንዳሉ አረፉ። ኢ.ሕ.አ.ፓ ታሪክ ሆነ። ኢ.ሕ.አ.ፓ ትዝታ ሆነ።

የ"ያ ትውልድ ተቋም" የኢ.ሕ.አ.ፓን 45ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ስናስብ ከጠንካራ ጅማሮው፣ ከውብ ሂደቱና፣ ከደካማው ጎኑ እየጨለፍን ያስነበብነው ጽሁፍ በገጠር በከተማ በኢ.ሕ.አ.ፓ የተለያዩ ክፍሎች ተሳትፈው መሥዋዕት ለሆኑት አባላቱና አባል ባይሆኑም የደርግ ቀይ ሽብር፣ ነፃ እርምጃና ቤት ለቤት አሰሳ ጨምሮ በተለያየ ጊዜና ምክንያት ለተረሸኑ ወገኖች ሁሉ ይሁንልን። ኢትዮጵያን በተለያየ ማኅበራዊ መልኩ ሲረዳና ሲያግዝ የነበረው ያ ትውልድ በተደራጀ መልኩ ኢ.ሕ.አ.ፓን መሥርቶ ጅምሩ ፍጻሜ ለሆነባቸው አመራር አካሉና አባላቱ ያለንን ክብር እንገልጻለን።

ኢ.ሕ.አ.ፓ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወትና የትግል ታሪክ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ፓርቲ እንደመሆኑ በሆነው ባልሆነው ታሪኩን ጥላሸት ቀቢዎችን በመከላከል የ"ያ ትውልድ ተቋም" መረጃ የማሰባሰብ ጉዟችን ውስጥ ኢ.ሕ.አ.ፓና የቀይ ሽብር ሰማዕታት ከተራራው ጫፍ ናቸውና ድጋፋችሁና ትብብራችሁ አይለየን እንላለን። "ያ ትውልድ ተቋም"ን በገንዘብ፣ በመረጃ፣ በሥራ፣ በሀሳብ፣ ወዘተ. ማገዝ ማለት በተለያየ ወቅት በደርግ የተረሸኑ ሰማዕታት ልጆቻችሁን፣ ወንድም እህቶቻችሁን፣ በጥቅሉ የያ ትውልድ ወገኖችን መርዳትና ማሰብ መሆኑን በመገንዘብ የያ ትውልድ ቤተሰቦች ትብብራችሁና እገዛችሁ አይለየን እንላለን።

ክብር ለቀይ ሽብር ሰማዕታት!!!
የያ ትውልድ ታሪክ ሕያው ነው!!!
ኢ.ሕ.አ.ፓ የትግል ትምህርት ቤት!!!


- ስልክ ፡ (703) 300 4302
- ኢሜል ፡ yatewlid@gmail.com,
- ድረ ገጽ ፡ http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org
- ምስለ ገጽ ፡ https://www.facebook.com/yatewlid.thegeneration/